# የአረንጓዴው ልማት አቅጣጫ ቀያሹ መሐንዲስ ሲዘከሩ

**ዘአማን በላይ**

bzaman@yahoo.com

ጊዜው እንዴት ይሮጣል ጃል?!–እነሆ ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊን በመስዕዋትነት ካጣናቸው አንድ ዓመት ሊሞላን ነው። ጊዜ ትናንትን በነበርነት ትቶ ባለ ራዕዩ መሪያችንን ካሳጣን 12 ወራቶችን ሊደፍን ነው። ታዲያ ይህ ከልካይ የሌለው ተፈጥሮአዊ ዑደት እንዳሻው ቢከንፍም፤ አቶ መለስ ለሀገራችን ትተውት የሄዱት ትውልድ ተሻጋሪ የገዘፈ ራዕይ ዛሬም እንደ መሪ የባቡር ፉርጎ ከእኛው ጋር አብሮን ተቀጣጥሎና እኛኑ አስከትሎ በልማት ጎዳና ላይ ሽምጥ መጋለቡን አልተወም–የድህነትን ተራራ እየናደና የብልፅግናን በር ወለል አድርጎ ለመክፈት እየታገለ። ታዲያ የብልሁና የአስተዋዩ መሪያችን ራዕዮች ከእኛ አልፈው የአፍሪካ ሞዴል በመሆናቸው፤ ተመፅዋችነትን እየተፀየፍን የብልፅግናው ማማ ላይ የማንወጣበት ምንም ምክንያት አይመስለኝም–እየተመራን የመጣንባቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም በአማካይ 10 በመቶ የዕድገት መሰላል ላይ ይዘውን ወጥተዋልና። ነገም እንዲሁ መሆኑ አይቀሬ ነው። ነገሩ "የነብርን ጭራ አይዙም፣ ከያዙም አይለቁም" እንዲሉት ነውና።




እርግጥ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ክስተት ከሆነው ሞት አያመልጥም። ትልቁ ቁም ነገር በህይወት ዘመኑ ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ዕድገት የሰራው ታሪኩ ነው። ከዚህ አኳያ አቶ መለስ የህይወት ዘመናቸውን በሙሉ ለህዝብ የኖሩ ብቻ ሳይሆኑ፣ ለእኛና ለመጪው ትውልድ ትተውልን የሄዱት ታላላቅ ስራዎቻቸው የሀገራችንን አስከፊ የድህነት ታሪክ በመለወጥ ላይ ያሉና ወደፊትም የሚለውጡ ናቸው። ሀገራችንም ሆነ ዜጓቿ መቼም የሚረሷቸው አይደሉም። አዎ! ሁሌም ከህሊናችን ጓዳ ውስጥ አይጠፉም–የነገ ሰው መሆን እንዴት እንደሚቻል ያስተማሩን በመሆናቸውም፤ "ነገነታችንን" ስናሰብ ሁሌም እናስባቸዋለን፤ እናስታውሳቸዋለን።

እናም እኔ የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ ምንም እንኳን በዚህች አጭር መጣጥፌ ስለ ታላቁ መሪ ፈርጀ ብዙ ውለታዎች የመፃፍ አቅሙ ባይኖረኝም፤ ለእኛና ለአፍሪካ ብሎም ለዓለም ካበረከቷቸው በርካታ ገፀ-በረከቶች መካከል አንዱ የሆነውን የአረንጓዴ ልማት አቅጣጫቸውና በሌሎች ተግባሮቻቸው በጥቂቱም ቢሆን እንዲህ ልዘክራቸው ወደድኩ። መልካም ንባብ።...

እንደሚታወቀው የብሩህ አዕምሮ ባለቤት የነበሩት እኚህ ታላቅ መሪ በየጊዜው አዳዲስ ሃሳቦችን እያፈለቁ ለሀገራችንና ለዓለም ሲያበረክቱ ነበር ፡፡ በዚህም የመላው አፍሪካ ድምፅ በመሆን ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ወደ ማግኘትም የተሸጋገሩ ነበሩ፡፡ አቶ መለስ አፍሪካውያን በመሠረታዊ የጋራ ጥቅም ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም እንዲወስዱ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ የአህጉሪቱ ቃል አቀባይ ሆነው ውጤት ማስገኘት የቻሉ ጀግና ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ በተለይም በየዓመቱ በአማካይ በሁለት ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ይጨምራል ተብሎ በሚጠበቀው ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ “አፍሪካ ዋነኛዋ ተጎጂ ናት” በማለት የምዕራቡ ዓለም በኢንዱስትሪ ሳቢያ ለፈጠረው የካርቦን ልቀት ለአህጉሪቱ ካሣ እንዲከፍል በመጠየቅ ከአፍሪካ ህዝቦች ባሻገር፤ ከራሳቸው ካደጉት ሀገራት ጭምር አንቱታን ለማትረፍ የበቁ የሀገራችን ዕንቁ ሰው ነበሩ፡፡

በዚህም በኮፐንሃገን፣ በሜክሲኮ...ወዘተ በተካሄዱ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔዎች፤ አፍሪካ በለውጡ ይበልጥ ተጎጂ የሆነችው የአየር ንብረቷ ተጋላጭ፣ ለውጡን ለመቋቋም ያላት ገንዘብና ቴክኖሎጂ ውስን እንዲሁም አህጉሪቱ ዕድገቷን በአዲስ አማራጭ ቴክኖሎጂ ዙሪያ ለመገንባት ያላት አቅም ከበለጸጉት ሀገሮች በእያሌው ያነሰ መሆኑን በማስረዳት በብርቱው የተከራከሩና አበረታች ውጤት ያመጡ ናቸው፡፡

በዚህ ተግባራቸውም የአፍሪካ አለኝታና መከታ መሆናቸውን በአደባባይ አስመስክረዋል፡፡ ይህን እምቅ አቅማቸውንና ክሂላቸውን የተገነዘበው ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለይም የበለፀጉት ሀገራት በቡድን ስምንት እና በቡድን 20 ስብሰባዎች ላይ ከሚገኙት በጣት የሚቆጠሩ የአፍሪካ መሪዎች ውስጥ በቀዳሚነት የሚጋበዙ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ እናም ቀደም ሲል በረሃብና በጦርነት የምትታወቀውን ሀገራችንን ስም በአዲስ የዲፕሎማሲ መንገድ አራማጅነት እንዲቀየር ለማድረግ የቻሉ የሀገራችንና የአፍሪካ ባለውለታ ናቸው፡፡ ከሁሉም በላይ የተጠቀሰውን የካርቦን ልቀት ችግርን ለመቋቋም “አረንጓዴ ልማት” የሚል አቅጣጫን በመቀየስ ሌሎች ሀገራት ከኢትዮጵያ ይህንኑ የካርቦን ልቀት መከላከያ ዘዴን እንዲወስዱ ያደረጉ ባለ ራዕይ መሪ ነበሩ፡፡

ሩቅ አሳቢው መለስ ሀገራችን እ.ኤ.አ በ2025 ትርፍ ካርቦን የማትለቅበት ደረጃ ላይ እንድትደርስ ሲያልሙ ነበር፡፡ ታዲያ ይህ የአቶ መለስ የሀገራችን ካርቦንዳይ ኦክሳይድን በዜሮ የመልቀቅ ግብ (Zero net emission)፤ አይቀሬው የአየር ንብረት ለውጥ ሊፈጥር የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ የሚያስችል ይዘት ያለው ነው። ይህ የአረንጓዴው ልማት ዕቅዳቸውም ኢትዮጵያ

የኤሌክትሪክ ኃይልን በሰፊው አምርታ ከሚያስፈልጋት በላይ የሆነውን ኃይል ለጎረቤት ሀገር የመሸጥ፣ ነዳጅን ከዕፅዋት የማምረት ስትራቴጂን እንድትከተል እንዲሁም ካርቦንን ከአየር የመምጠጥ አቅሟ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር ለማድረግ ያለሙ ግቦች ያለው ነው፡፡ እስቲ ለውድ አንባቢዎቼ ግልፅ ይሆኑ ዘንድ እነዚህን ግቦች ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው።...

እንደሚታወቀው በአቶ መለስ የተቀየሰው አረንጓዴው የልማት አቅጣጫ የሀገራችንን ሰፊ የሃይድሮ ፓወር እምቅ አቅም በመጠቀም የኤሌክትሪክ ኃይልን ከታዳሽ ምንጮች በሰፊው በማምረት ከፍጆታችን ትርፍ የሆነውን ለጎረቤት ሀገሮች ለመሸጥ ያለመና እንቅስቃሴውም የተጀመረ ነው። በዚህ መሰረትም ከነፋስ ጂኦተርማል፣ ከስኳር ተረፈ ምርትና በትንሹም ቢሆን ከፀሐይ ኃይል የማመንጨት ስራ እየተከናወነ ነው። ከዚህ መሳ ለመሳም የኃይል አጠቃቀማችንን ለመቆጠብ የማስተሳሰሪያና የማከፋፈያ መስመሮችን የመዘርጋት ተግባራት ገቢራዊ በመሆን ላይ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም ለባቡር ትራንስፖርት ጭምር የምንጠቀምበት ስልት በአቅጣጫው ላይ ተቀምጧል። በእነዚህ ሂደቶችም ምንም ካርቦንዳይ ኦክሳይድ በማይለቅ አኳኋን የኤሌክትሪክ ኃይልን በሰፊው ለማመንጨት ታስቦ ገቢራዊ እየሆነ ነው። እንግዲህ በታላቁ መሪያችን የተቀመረው ይህ አካሄድ ከአረንጓዴነቱ ባሻገር ያለንን ሃብት በአግባቡ እንድንጠቀም የሚያደርግ ብሎን ከውጭ የምናስገባውን ውድ ነዳጅ ለማስቀረት የሚያግዝ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።

በልማት አቅጣጫው መሰረት ነዳጅን ከዕፅዋት ማምረትን በተመለከተም፤ ምንም እንኳን ዘርፉ በአሁኑ ወቅት ጅምር ቢሆንም በመጪዎቹ ዓመታት በከፍተኛ መጠን ሊሻሻል የሚችል ነው። እርግጥ የስኳር ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ለማስፋፋት የታሰበው ተረፈ-ምርቱ ነዳጅን የሚተካ ኤታኖልና ኤሌክትሪክን ማመንጨት እንዲያስችል ለማድረግ ነው—ሌሎች ፋይዳዎቹ እንደተጠበቁ ሆነው። ከዚህ ጎን ለጎንም የሀገራችን የደን ግብርና ስራ ናፍጣን የሚተካ ምርትን ለማምረት የሚያስችሉን ተክሎችን ያከተተ እንዲሆን ተደርጓል። ታዲያ ይህ አሰራርም ከአየር ንብረት ለውጥ ፋይዳው በተጨማሪ ከውጭ የምናስመጣውን ነዳጅ እዚሁ ሀገራችን ውስጥ በቀላሉ ማምረት የሚያስችለን መሆኑን ውድ አንባቢዎቼ ልብ ይሏል!

ካርቦንዳይ ኦክሳይድን ከአየር የመምጠጥ አቅማችንን ከመጨመር አኳያም አቶ መለስ የነደፉት የአረንጓዴ ልማት አቅጣጫ ከታዳሽ ምንጮች በተጨማሪ የምንጠቀምባቸውን የአላቂ ምንጮችን ታሳቢ ያደረገ ነው። እርግጥ በተለያዩ ምክንያቶች እንደ ድንጋይ ከሰል ያሉትን ምርቶችን መጠቀማችን አይቀርም። በመሆኑም እንደ ሀገር የካርቦን ልቀታችንን ዜሮ ለማድረግ የለቀቅነውን መጠን መልሰን መምጠጥ ይኖርብናል። ለዚህም የደን ተከላን በማስፋፋትና

በመንከባከብ ካርቦንን ይበልጥ የመምጠጥ ስራዎች ይከናወናሉ። ሁሉም ሰው ደን ይትከልና ይንከባከብ የሚባለውም ለዚህ ነው።

ታዲያ እዚህ ላይ አቶ መለስ የካርቦን ልቀት ያሳሰባቸውና የአረንጓዴ ልማት አቅጣጫን ለመቀመር የተነሳሱት ያለ ምክንያት እንዳልነበረ ውድ አንባቢዎቼ ልብ ሊሉልኝ ይገባል። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት የዓለም ሙቀት በአማካይ ቢያንስ በሁለት ዲግሪ ሴንቲግሬድ መጨመሩ አይቀርም። ይህ ደግሞ በሀገራችንም ይሁን በአፍሪካ ብሎም በዓለም አየር ንብረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳረፉ አይቀሬ ነው። በተለይም ችግሩ በኢትዮጵያ ላይ የሚያስትለው ተፅዕኖ ከሙቀት መጨመርና ከዝናብ መጠን ስርጭት ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው። እናም ሙቀት ሲጨምር እንደ ወባ ያሉ የቆላ በሽታዎች ወደ ደጋውም ሊዛመቱ ይችላሉ። የዝናብ መጨመር ደግሞ ስርጭቱ የባሰውን አስተማማኝ የማይሆንበትን ሁኔታ በመፍጠር በሀገራችን ግብርና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋል። የጎርፍና የድርቅ መፈራረቅን ሊያስከትል ይችላል።...እንግዲህ እነዚህ ከሀገራችን አንፃር የተመለከትናቸው የካርቦን ተፅዕኖዎች ናቸው—ታላቁ መሪያችን "የአረንጓዴን ልማት" አቅጣጫ ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካና ለዓለም ያበረከቱት።

ይህ የአቶ መለስ "የአረንጓዴ ልማት" አቅጣጫ በአፍሪካም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ከማግኘቱም በላይ፤ በርካታ ሀገሮች የልማት አቅጣጫውን በመውሰድ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ የታላቁ መሪያችን ብሩህ አዕምሮ ያፈለቀው ይህ የልማት አቅጣጫ ትናንት በረሃብና በድርቅ የምትታወቀውን ሀገራችን፤ ዛሬ ለድርቅና ረሃብ መባባስ ምክንያት የሆነውን የካርቦን ልቀት ለመቋቋም የመፍትሔው አካል ሆና እንድትታይ ያደረገ ወደር የማይገኝለት ምጡቅ ተግባር ነው— ከትናንት የድርቅ ተጠቂነት ወደ ዛሬ የድርቅ መፍትሔ አመላካችነት የዘለቀ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ድል፡፡...ከአንድ የሀገር ገፅታ ግንባታ ጫፍ ወደ ሌላኛው ያሸጋገሩን ብልህ መሪ።...

...እስቲ አሁን ደግሞ ወትሮም ግጭትና አለመረጋጋት በማይለየው የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ካበረከቱት ወደር የሌለው ተግባራቸው እናምራ፡፡ አቶ መለስ የኤርትራ መንግሥት ሀገራችንንና ምስራቅ አፍሪካን የጦርነት አውድማ ለማድረግ የቀመረውን የሽብር ስትራቴጂ በቅርበት በመከታተልና ብቃትና ብስለት ባለው ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ እየተመሩ የአስመራው አስተዳደር ለመፍጠር የሞከረውን ቀጣናዊ ቀውስ ለማርገብ በቁርጠኝነት የሰሩ አፍሪካዊ አባት ናቸው፡፡ ላለፉት 40 እና 50 ዓመታት ሰብዓዊ ጥፋት ያስከተሉ ጦርነቶች የተካሄዱበትን ይህን ቀጣና ማረጋጋት ቀላል ባይሆንም፤ ታላቁ መሪያችን ግን ለሰላምና መረጋጋት ጠንቅ የሆኑ አካሄዶችን በሳል በሆነና ብቃት ባለው አካሄድ እየተመሩ ያጋጥሙ የነበሩ ፈተናዎችን በድል ተወጥተዋል፡፡

አቶ መለስ አሸባሪነትና አክራሪነት በቀጣናው እንዳያቆጠቁጥና ምስራቅ አፍሪካ ከፅንፈኞች ስጋት ነፃ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉ መሪ ናቸው፡፡ ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት መንግሥት

አልባ በነበረችው ሶማሊያ የመሸገው “እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት” በወቅቱ በሀገራችን ላይ ደቅኖት የነበረውን ግልፅና ድርስ አደጋ ብሎም በምስራቅ አፍሪካ  ሰማይ ላይ እንዲያንዣብብ ያደረገውን የጦርነት ደመና ብስለት በተሞላው ዘዴ አስወግደዋል፡፡ በወቅቱ የኢጋድ አባል ሀገራትንና አፍሪካ ህብረትን ከጎናቸው በማሰለፍ የሶማሊያ አክራሪ ፅንፈኞች አከርካሪያቸው እንዲሰበር ለማድረግ ችለዋል፡፡ በዚህም በአንድ መልኩ እንደ መንግሥት በአስተማማኝ ዲፕሎማሲ የሚመሩ መሆናቸውን ያረጋገጡ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ መከላከያሠራዊታችን ማንኛውንም ግዳጅ በብቃት መፈጸም የሚችል ቁመና እንዳለው ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማሳወቅ አስተማማኝ ወታደራዊ ዲፕሎማሲ መገንባት የቻሉ መሪ ናቸው፡፡

ራሱን “አል-ሸባብ” እያለ የሚጠራው የሶማሊያ ሽብርተኞች ቡድን በቀጣናው ሰላምን ለማናጋት ያደረገውን አፍራሽ እንቅስቃሴን ፈጥነው በመረዳትም፤ ከምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) ጋር በመሆን ወሳኝ ድርሻ አበርክተዋል፡፡ በዚህ ረገድ በኢጋድና በአፍሪካ ህብረት ውስጥ ባከናወኑት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራዎች፤ ሌሎች ሀገራትም ሠራዊታቸውን ወደ ሶማሊያ እንዲልኩ የማግባባት ተግባራትን ፈጽመዋል፡፡ ከዚህ ባሻገርም፤ በዚያች ሀገር ውስጥ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍንና ቋሚ መንግሥት እንዲፈጠር ሌት ተቀን ሲሰሩ ነበር፡፡ በዚህም ዛሬ ሶማሊያውያን ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲያካሂዱ ጥርጊያ መንገድ በማመቻቸት አቶ መለስ ወደር የሌለው ሚና ተጫውተዋል፡፡

ከሁሉም ጎረቤት ሀገሮች ጋር በሰላም፣ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ለመፍጠር ደፋ ቀና ይሉ የነበሩት እኚህ ታላቅ የአፍሪካ ልጅ፤ ለየትኛውም ወገን የማይወግን መርሃዊ አካሄዳቸውን በመጠቀም ደቡብና ሰሜን ሱዳን ችግራቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ አስችለዋል፡፡፡ ባላቸው ለማንም ያልወገነ አቋም በሁለቱም ሱዳኖች እኩል ተቀባይነት የነበራቸው እኚህ መሪ፤ በመንግሥታቱ ድርጅት ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሁለቱም ሱዳኖች የኢትዮጵያን መከላከያ ሠራዊት እንዲመርጡ ምቹ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ዲፕሎማሲን መፍጠር የቻሉ ናቸው፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ አቶ መለስ በሱዳን - ዳርፉር የተፈጠረውን ቀውስ ለማርገብ የሱዳን መንግሥትና የደቡብ ሱዳን ነፃነት ንቅናቄ መካከል “ሁሉን አቀፍ የሰላም ስምምነት” /Comprehensive Peace Agreement ‘CPA’/ እየተባለ የሚጠራውን ሰነድ እንዲፈራረሙ ብርቱ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አድርገዋል፡፡ ከዚህ በላይም፤ ለሰላም ካላቸው ፅኑ ፍላጎት በመነሳት በዳርፉር የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ ህብረት ተልዕኮ (UNAMID) ጥላ ስር የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በሰላም አስከባሪነት እንዲሰማራ በማድረግ በዚያች ሀገር መረጋጋት እንዲፈጠር ጥረዋል፡፡

እናም በእነዚህ ቀጣናዊ ተግባሮቻቸው በአፍሪካ ህዝቦች ዘንድ ታላቅ አክብሮትን ማግኘት የቻሉ አርቆ አስተዋይ መሪ ናቸው፡፡

ከታላቁ መሪያችን የዲፕሎማሲ ተግባራት ውስጥ የማይረሳው ሌላኛው ታላቅ ክንዋኔ “የሰላም ዲፕሎማሲ” አንዱ ነው፡፡ አቶ መለስ በህይወት በነበሩበት የመሪነት ዘመናቸው ሀገራችን ለአፍሪካ ሰላም መከበር በቁርጠኝነት እንድትንቀሳቀስ ያስቻሉ ናቸው፡፡ ለ21 ዓመታት ኢትዮጵያን ሲመሩ በሩዋንዳ፣ በብሩንዲ፣ በላይቤሪያና በሱዳን ዳርፉርና በአብዬ ግዛቶች መከላከያ ሠራዊታችንን በማሰማራት ለአፍሪካውያን ሰላም መረጋገጥ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ የተጉ የአፍሪካዊያን ተቆርቋሪ ነበሩ፡፡ በእርሳቸው አመራር ሰጪነት የተሰማራው ሠራዊታችንም የተሰጠውን ግዳጅ በብቃትና በፍጹም ወታደራዊ ዲስፕሊን በመታገዝ የአፍሪካውያን ኩራት መሆኑን በተግባር አረጋግጧል፡፡

እርግጥ እኚህ ባለራዕይ፣ የአፍሪካ ኩራትና ዲፕሎማት እንዲሁም ዓለምን ያስደመሙ በሳልና አርቆ አስተዋይ መሪ ዛሬ በህይወት የሉም፡፡ ይሁንና የሀገራችንን ስም በዓለም አደባባይ የማደስ፣ የአፍሪካን ዘላቂ ጥቅሞች የማስጠበቅ እንዲሁም ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ገንቢ ሃሳቦችን የማቅረብ ህልቆ መሳፍርት የሌላቸው ሥራዎቻቸው ግን ዛሬም ከእኛ ጋር ናቸው፡፡ አዎ! አቶ መለስ እውነትን፣ ትዕግስትን፣ አስተዋይነትን፣ ፅናትን፣ ሰላምን፣ ልማትንና ዴሞክራሲን ተዝቆ ከማያልቀው ዕውቀታቸው ሳይሰስቱ አስተምረውናል። ሰው የመሆን ፊደልን አስቆጥረውናል። የውርደታችንን ካባ ገፍፈው ቀና ብለን እንድንሄድ አድርገውናል። …ሌላ ሌላም።…

…እናስ?...እናማ እናመሰግናቸዋለን። እንወዳቸዋለን። ሁሌም በልባችን ማህደር ውስጥ ከትመናቸው እንዘክራቸዋለን። እርግጥ አርቆ አሳቢው መሪ በሞት ሲለዩን እርሳቸው ያቀበሉንን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ አጭር ሩጫ ዱላ ተቀብለን ራዕያቸውን ዕውን ለማድረግ በእልህና በወኔ ውስጥ ሆነን ነው። ይሁንና ህልፈታቸው አንዴ የሆነ ነውና የመንፈስ ልጆቻቸው ሆነን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ትልሞቻቸውን በእልህ ሰንቀንና የላቀ ውጤት አስመዝግበን ራዕያቸውን ከግቡ በማድረስ ሞታቸውን እረፍት ማድረጋችን አይቀሬ ነው።

አዎ! የአቶ መለስን አሻራ ተከትለን ውጥኖቻቸውን ግብ እንዲመቱ ለማድረግ የበኩላችንን ከተወጣን ከሃዘናችን ወጥተን በድሎቹ ፋናዎች መድመቃችን አይቀርም። ታዲያ ከእኛ የሚጠበቀው ታላቁ መሪ ብዙ በደከሙለት፣ መሰረቱ በፀናውና ምንግዜም በማይናወጠው መስመር ተጉዘን ረጅሙን የዕድገት አቀበት በቁርጠኝነት መወጣት ነው።እርግጥም ዛሬ በህይወት የሌሉት አቶ መለስ ናቸው። መርሃቸውና የደከሙለት ትክክለኛ መንገድ ግን አብሮን አለ። ህልማቸው አይከስምም። ከእኛ ጋር ይዘልቃል፣ ከትውልድና ከዘመን ጋር አብሮን ይሻገራል። ብልሁ መሪ

በአካል ቢለዩንም፣ መንፈሳቸው ግን ከእኛ ጋር ነው። እናም ከእኛ የሚጠበቀው የአቶ መለስን አንፀባራቂ ራዕይ ዱካን መከተልና እንዳይቀለበስ ማድረግ ብቻ ነው።

ይህን ስንከውንም የአቶ መለስን ህልም በሰላማችን፣ በልማታችንና በዴሞክራሲያችን እንመነዝረዋለን። ሌሎች ሀገሮች የደረሱበት የዕድገት ማማ ላይም እንወጣለን። ለዚህም ሁሌም በተሰማራንበት የስራ መስክ “የድህነት ተራራ የሚናደው በዕውቀት ጥይት ነው” የሚለውን የታላቁን መሪያችንን አባባል ማስታወስ ይኖርብናል—ምርኩዛችን እርሱው ነውና። ቸር እንሰንብት።

“ራዕይህ በእኛ በመንፈስ ልጆችህ ዕውን ይሆናል!”